| መመሪያ/ደንብ | MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS<br>ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) |
|---|---|

ከዚህ ጋር አግባብ ያላቸው **ምንጮች**፦ ABA, ABC, ABC-RA, ACA, ACD, ACG, ACG-RA, ACG-RB, DNA, ECM, ECM-RA, FAA, JEE, JEE-RA

ኃላፊ ጽ/ቤት፣- ዋና የሥራ ኃላፊ/Chief Operating Officer

# የትምህርት መገልገያዎች እቅድ

I. ዓላማ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ (Policy FAA) የትምህርታዊ ፋሲሊቲዎችን እቅድ/Educational Facilities Planning ለመተግበር

የፋሲሊቲዎችን አቅም የማሳደግ ፍላጎትን ምላሽ ለመስጠት፣ የቦታ መረጣን ጨምሮ፣ የትምህርት ቤት ድንበሮች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ እና የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ጥምረት የካፒታል ኢንቨስትመንት ፕሮግራም (CIP) የማሳደግ ሂደት፣ የትምህርት ፋሲሊቲዎች ማስተር ፕላን፣ እና ካፒታል ያልሆነ ስትራተጂዎችን/non-capital strategies መተለም

II. ቀደምት መነሻ

በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ላይ እንደተደነገገው፣ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning፣ አካል የሚያካትተው -

A. ስለተማሪ ምዝገባ የሚጠበቅ ግምት እና የትምህርት ፋሲሊቲዎች እና የህንፃ ሲስተሞችን አካላዊ ሁኔታ ተከታታይ ትንታኔ/ግምገማ፣

B. በፋሲሊቲ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ፤ እና

C. ምላሽ ሰጪ አማራጮችን የሚፈጥሩ እና ወደ ትክክለኛና ፍትኃዊ የፋይናንስ ኃላፊነት እና ትምህርታዊ ትርጉም ያላቸው ውሳኔዎች የሚመራ የዉሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ፣ ከአካባቢ፣ ከስቴት፣ እና ከፌደራል መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ፣ የቦርድን ፍትሃዊነት፣ሚዛናዊነት ፖሊሲን/Board Policy, ACA Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency ግምት ውስጥ ያስገባ።

III. ትርጉሞች

አዋሳኝ ትምህርት ቤቶች ማለት፦ ቢያንስ፣ በተፋሰሱ አካባቢ ውስጥ ያሉ ቅርበት ያላቸዉ ትምህርት ቤቶች።

A. የካፒታል ባጀት ማለት፦ ለካፒታል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተመደበ ዓመታዊ ባጀት ነው።

B. የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም (CIP) ለካፒታል ማሻሻያዎች የሚውል የስድስት-ዓመት አጠቃላይ የወጪ እቅድ ነው። CIP የቦታ ግኝት፣ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ግንባታ፣ እና የህዝብ ትምህርት ቤቶች ፋስሊቲዎች ጥገና፣ ካውንቲ አቀፍ ስርዓታዊ የፕሮጀክቶች እና ትላልቅ ካፒታል ፕሮጀክቶችን ያካተተ በመተካት ላይ ያተኩራል። በእያንዳንዱ የጎደሎ ቁጥር የበጀት ኣመት የሚጀምር ለስድስት ኣመት ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነዉ CIP በየሁለት-ኣመት ሂደት ተገምግሞ ይፀድቃል። ለባለሙሉ ቁጥር የባጀት ኣመቶች፣ በፀደቀው CIP ተፈላጊ ለውጦች ለባለ-ስድስት-ኣመት የ CIP ወቅት መሻሻያ ለውጦች በሁለተኛው ኣመት እንዲታዩ ይደረጋል።

C. የከተማ አስተዳደር ቡድኖች ማለት ዜጋ፣ የቤት ባለቤት፣ ጎረቤት፣ ወይም በሜሪላንድ ብሔራዊ ካፒታል ፓርክ እና ፕላን

ኮሚሽን (M-NCPPC) ወይም በሞንትጎመሪ ሪጅናል አገልግሎት ማእከሎች የተመዘገቡ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት ነው።

D. ክለስተር/Cluster የሁለተኛ ደረጃ፣ ኤለመንተሪ/አንደኛ ደረጃ/፣ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያካተተ ሲሆን ወደዚያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚልኩ ግልጽ የሆነ ጂኦግራፊያዊ የትምህርት ቤቶች ምደባ ማለት ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተከፋፈለ የምደባ ይዘት አላቸው፣ እና በአንድ ወይም የበለጠ ክለስተሮች ዉስጥ አንዳንድ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተከፋፈለ የምደባ ይዘት አላቸው።

E. ኮንሰርሽየም/Consortium ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ወይም መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እንደየቅርበታቸው ተማሪዎች በተወሰነ አይነት የትምህርት አሰጣጥ ወይም ትኩረት በሚመርጡት ቦታ የሚማሩበትን እድል ለመስጠት በቡድን ማካለል ነው።

F. የፋሲሊቲ ዲዛይን እስከ ትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ግንባታ ድረስ ያሉትን ሁሉንም የእቅድ እና የዲዛይን ሂደቶችን ያቅፋል። እንደየሁነቶቹ ቅደምተከተል፣ የፋሲሊቲ ዲዛይን አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፦

1. የትምህርት ዝርዝሮች የሚገልጹት የማስተማር ፕሮግራምን ለመደገፍ ምን ያህል ቦታ እንደሚያስፈልግና ስለህንጻው አቀማመጥ እና ዲዛይን ዝግጅት የንድፍ ባለሙያን ይመራል።

2. የአዋጭነት ጥናት ስለ ፕሮጀክት መጠን እና የዋጋ ግምት የሚገልጽ ሲሆን፣ ስለ ፋሲሊቲ ዲዛይን ዝርዝር አይኖረውም።

3. ስዕላዊ ንድፍ/Schematic design ማለት ጽንሰ ሐሳቦችን ለትምህርት ቤቱ የመነሻ እቅድ የሚገምግም እና የሚያዳብር የዲዛይን የመጀመሪያው ምዕራፍ አካል ነው።

4. የመጀመሪያው እቅድ አጠቃላይ መጠን፣ ስፋት፣ ሚዛን፣ የሥራ ተያያዥነት፣ የትራፊክ ፍሰት፣ እና የፕሮጀክቱ አካል ዋጋ ይዘረዝራል/ይገልጻል። ፅንሰሃሳባዊው ንድፍ ለማሻሻል ስለታሰበው ፋሲሊቲ ውስጣዊ እና ውጫዊ ቦታዎች ፅንሰሃሳባዊ ቅንጅት፣ ውስጣዊና ውጫዊ ቁሳቁሶች አጠቃቀም፣ እና የውቅር አመራረጥ፣ መካኒካል፣ የቧንቧ ስራዎች፣ እና ስለ ኤሌክትሪካል ሲስተም ፅንሰሃሳቦችን አጠቃላይ ገጽታ በግልጽ ያስተላልፋል። የመጀመሪያው ፕላን ለቦርድ ቀርቦ ይፀድቃል።

5. ዲዛይን ማዳበር ማለት፦ የአርኪቴክቸራል እቅዶችን የማጣራት እና የፕሮጀክቱን መካኒካል፣ ኤሌክትሪካል፣ እና የቧምቧ ስራዎችን ሲስተም የመሣሰሉትን የፕሮጀክቱ ኢንፍራስትራክቸር ስራዎች የሚዳብሩበት ደረጃ ነው።

6. የግንባታ ሠነዶች ፋሲሊቲውን ለመገንባት የተዘጋጁ በንድፍ ስራዎቹ ውስጥ የተካተቱ የግንባታ ዝርዝሮችን ፋሲሊቲውን ለመገንባት እንደ ኮንትራት ሠነድነት የሚያገለግሉ ዝርዝር ሠነዶች ይኖሩታል።

H. በስነምድራዊ አቀማመጥ/ጂኦግራፊያዊ በተማሪ ምርጫ የሚደረግ ምደባ እቅዶች የትምህርት ፕሮግራም አሰጣጥ ወይም ትኩረት ላይ ተመስርቶ ተማሪዎች ለትምህርት ቤት ምደባ የሚመርጧቸውን ጂኦግራፊያዊ አካባቢ(ዎችን) ይለያል። እነዚህ ጂዮግራፊያዊ መስኮች፣ በተወሰኑት መስፈርቶች መሰረት ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ የመከታተል ዋስትና ሊያገኙ የሚችሉባቸው "base areas/መሰረታዊ ቦታዎች" ተብለው የሚጠሩ መስኮችን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ወይም መስኩ ለግላዊ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ ምድብ የሌለው አንድ ነጠላ ቦታ ሊሆን ይችላል።

I. የወላጅ፣ መምህር፣ (ተማሪ) ህብረት (PT(S)As) የሞንትጎመሪ ካውንቲ የወላጅ መምህር ህብረት ካውንስል/Montgomery County Council of Parent Teacher Associations, Inc. (MCCPTA) አባል ቡድኖች ናቸው። በተጨማሪም፣ PT(S)A ሳይኖር፣ የወላጆች/ሞግዚቶች፣ መምህራን፣ እና ተማሪዎች ድርጅት PT(S)A ን በመተካት በትምህርት ቤት የሚንቀሳቀስ/የሚሰራ ነው።

J. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ ለቦርድ ፖሊሲ Board Policy FAA ዓላማ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning እና ይህ ደንብ ስለፋሲሊቲ እቅድ አማራጮችን የባለድርሻ አካላትን ሰፊ ተሳትፎ በማካተት በዚህ ሳይወሰን፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ የማህበረሰብ አባላት እና ድርጅቶች፣ እና የአካባቢ አስተዳደር

ኤጀንሲዎች፣ በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ABA መሠረት የማህበረሰብ ተሳትፎ/Community Involvement እና የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA፣ ስለ ትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳት እና ለቦርዱ የማሳወቅ ሂደትን ያመለክታል ።

## IV. የፋሲሊቲዎች ፕላን ትንታኔ

የፋሲሊቲዎች እቅድ ሂደት በሚከተለው ይጀምራል፡-

### A. የተማሪ ምዝገባ እሳቤዎች

1. የተማሪ ምዝገባ ግምት እቅድ የሚዘጋጀው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፕላን መምሪያ የካውንቲ ህብረተሰብ ትንበያ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የእቅድ ምንጮች ጋር በመተባበር ነው።

2. በእያንዳንዱ ፎል፣ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የምዝገባ እሳቤዎች የሚዘጋጁት ለ ስድስት-ዓመት ጊዜ ነው። የረዥም-ጊዜ ትንበያዎች ታሳቢ የሚያደርጉት ለ10ኛ እና 15ኛ ዓመት በተከታታይ የሚገቡትን ታሳቢ በማድረግ ነው። የረዥም ጊዜ ትንበያዎች ዝርዝር ትንታኔ ክፍሎች ማለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ፣ እና ለኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች ክለስተር ወይም ኮንሰርሽየም ደረጃ ትንበያ ነው።

3. ትንበያዎችን ለማጥራት እና በአገልግሎት አሰጣጥ፣ ፕሮግራሞች፣ ወይም በሠራተኛ ምደባ ላይ ማናቸውንም ለውጦች ለማንፀባረቅ በየዓመቱ ኤፕሪል ወር ስለ ቀጣዩ የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት ምዝገባ ታሳቢ የተደረጉ ነገሮች ክለሳ ይደረጋል።

4. ስለ ተማሪ ምዝገባ ታሳቢ ለማድረግ ተግባር ላይ የዋለው ዘይቤ CIP እና የማስተር ፕላን ሠነዶች አባሪ ተደርገዋል።

5. የሚፈልጉ/የሚመርጡ ተመዝጋቢዎችን ብዛት፣ ክልል፣ ትምህርት ቤት ገብተው የሚከታተሉ ተማሪዎችን በሙሉ ያካትታል።

   a) ለ ት/ቤት የሚፈለግ/የሚመረጥ የተመዝጋቢዎች ብዛት ክልል—

      (1) ከ 450 እስከ 750 ተማሪዎችን በኤለመንተሪ/አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣

      (2) ከ 750 እስከ 1,200 ተማሪዎችን በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እና

      (3) ከ 1,600 እስከ 2,400 ተማሪዎችን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች።

      (4) በልዩ ትምህርት እና ተለዋጭ ፕሮግራም ማእከሎች የምዝገባ ሁኔታ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የሚለይ ሲሆን በአጠቃላይ ዝቅተኛ ይሆናል።

   b) ስለ አዲስ ትምህርት ቤቶች ሲታቀድ ወይም ስለነባር ትምህርት ቤቶች የለውጥ አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ የተመዝጋቢዎች ብዛትና መጠን ግምት ውስጥ ይገባል። ሁኔታዎች ካስገደዱ ከተመራጭ የብዛት መጠን መለየት ሊኖር ይችላል።

6. የትምህርት ቤት ስብጥር እና የፋሲሊቲ ገጽታ

   a) የትምህርት ቤት ስብጥር አጭር ታሪክ የሚያካትተው የትምህርት ቤት ተማሪ ህብረተሰብን የዘር/የጎሳ ስብጥርን፣ የነፃ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ (FARMS) ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ፣ እና እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች (ESOL) ፕሮግራምን እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ መጠንን ነው።

b) የፋሲሊቲ ዘገባዎች የክፍል አጠቃቀም በፕሮግራም እና ስኩዌር ጫማ፣ የቦታ ስፋት፣ የተከፈተበት ዓመት፣ ለፓርክ ያለው ቅርበት እና ለማዘዋወር የሚያስችሉ ማስተማሪያ ክፍሎች ቁጥርን ያካትታል።

B. የትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች/Educational Program Requirements

1. በዋና የሥራ ኃላፊ ጽ/ቤት የሚሠሩ የ MCPS ሥራ ባልደረቦች በዋና የአካዳሚ ኃላፊ ጽ/ቤት እና ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት የትምህርት ፕሮግራም የሥራ ባልደረቦች ጋር ስለ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎችን ለመለየት በቅንጅት ይሠራሉ።

2. የታለመዉ የፕሮግራም መስፈርቶች የመማርያ ክፍል መጠን ለውጦችን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን እንደ ነባር፣ አዲስ፣ እና የታሰቡ ለውጦች የመሳሰሉ በትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የሚያስከትሉትን ተጽእኖዎች ግምት ውስጥ ያስገባሉ።

C. የፕሮግራም አቅም እሳቤዎች(ስሌቶች)/Program Capacity Calculations

1. የፕሮግራም መያዝ አቅም መጠን፥ በፋሲሊቲው ይካሄዳል ተብሎ በተገመተው የትምህርት ፕሮግራም መሠረት በፋሲሊቲው የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥርን ያመለክታል። የ MCPS የፕሮግራም ስፋት/መጠን የሚሰላው በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ጣቢያዎችን በእያንዳንዱ መመርያ ክፍል በተማሪ-ለ-መማርያ ክፍል እና ፕሮግራም ንጽፅር ውጤት ነው።

2. የ-ክፍል - ከተማሪ ብዛት ምጥጥን ዓመታዊ የሥራ ማስኬጃ ባጀት ሂደት ከሚወሰን ከሠራተኞች ምደባ ምጥጥን ጋር መጣረስ/መደናገር የለበትም።

3. በቦርድ ተግባር ላይ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የፕሮግራም አቅም/capacity እና ተዛማጅ የሆኑ የተማሪ - ለ- ክፍል ምጥጥን መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፦

ተማሪ-ለ-ክፍል የማመጣጠን መመሪያ

| ደረጃ | የተማሪ-ለ-መማርያ ክፍል ንፅፅሮች |
|---|---|
| ሄድ ስታርትና ቅድመ-ሙአለህፃናት | 40:1 (2 ክፍለ-ጊዜዎች በቀን) |
| ሄድ ስታርትና ቅድመ-ሙአለህፃናት | 20:1 (1 ክፍለ-ጊዜ በቀን) |
| K ክፍል/ሙአለህጻናት | 22:1 |
| K ክፍል-የተቀነሰ የክፍል መጠን | 18:1 |
| 1-2ኛ ክፍሎች—የተቀነሰ የክፍል መጠን | 18:1 |
| ከ1-5ኛ ክፍሎች ኤሌሜንታሪ | 23:1 |
| ክፍሎች፦ 6-8 መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>ክፍሎች፦ 9-12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 25:1[a]<br>25:1[b] |
| ልዩ ትምህርት/Special Education፣ እንግሊዝኛ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች/ESOL፣ አማራጭ ፕሮግራሞች/Alternative Programs | ከዚህ በታች “c”ን ይመልከቱ |

a) የፕሮግራም አቅም በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ የፕሮግራም አቅም እንቅፋቶችን በማስወገድ ይስተካከላል። 25 የመያዝ አቅም ያለው መደበኛ የመማርያ ክፍል እጅጉን ተመራጭ የሆነውን የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መገልገያ አጠቃቀም ለማንፀባረቅ በ.85 ይባዛል (ከ 21.25 ተማሪዎች በመማርያ ክፍል ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል)።

b) የፐሮግራም ኣቅም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ የፐሮግራም እንቅፋቶችን በማስወገድ ይስተካከላል። 25 የመያዝ አቅም ያለው መደበኛ የመማርያ ክፍል እጅጉን ተመራጭ የሆነውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መገልገያ አጠቃቀም ለማንፀባረቅ በ.90 ይባዛል (ከ22.5 ተማሪዎች በመማርያ ክፍል ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል)።

c) ልዩ ትምህርት፣ ESOL፣ ኣማራጭ ፐሮግራሞች፣ እና ሌሎች ልዩ ፕሮግራሞች ከተዘረዘሩት የተለዩ የመማርያ ክፍል ንጽጽሮች ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

D. የፋሲሊቲ አጠቃቀም ከፐሮግራም አቅም፣ ከስቴት ደረጃ አሰጣጥ አቅም፣ እና ለመቀበል/ለምዝገባ ተመራጭ ከሚሆነው አቅም መጠን ጋር በወቅቱ ያለውን የፋሲሊቲ አጠቃቀም እና የሚታለመውን የተማሪ ምዝገባ ትንተና ንጽጽርን ያመለክታል።

1. የፋሲሊቲ አጠቃቀም ደረጃ ከ80 ፐርሰንት ያነሰ እንደሆነ የትምህርት ቤት ጠቀሜታው አነስተኛ ነው ተብሎ ይታሰባል።

2. የፋሲሊቲ አጠቃቀም ደረጃ ከ100 ፐርሰንት የሚበልጥ ከሆነ የትምህርት ቤቱ አጠቃቀም ከመጠን በላይ እንደሆነ ይገመታል።

3. በልዩ ሁኔታ በቦርድ መመሪያ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ኤለመንተሪ፣ መካከለኛ ደረጃ፣ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፐሮግራም አቅም ከ80 እስከ 100 ፐርሰንት ዉስጥ ዉጤታማ የፋስሊቲ አጠቃቀም መተግበር አለበት።

   a) ከመጠን በላይ አጠቃቀምን በሚመለከት፣ አዲስ ግንባታ ከመታቀዱ አስቀድሞ የቦታው አጠቃቀም ለረዥም ጊዜ አስፈላጊ ስለ መሆኑ ለመገምገም ጥረት ይደረጋል።

   b) የፋሲሊቲዎች አጠቃቀም ዝቅተኛ የመሆንም ሁኔታ ከረዥም ጊዜ የምዝገባ ትንበያ አንፃር ይገመገማል።

4. የምዝገባ ሁኔታ እያደገ ሲሄድ ቋሚ የሆነ አቅም እስከሚኖር ድረስ ተንቀሳቃሽ የመማሪያ ክፍሎች በጊዜያዊነት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

5. ተንቀሳቃሽ የመማርያ ክፍሎች በተጨማሪ የልጆች እንክብካቤ ፕሮግራሞች በት/ቤት እንዲካሄድ ለማስቻል ሊያገለግሉ ይችላሉ፣ እና ሌሎች የማሟያ ተግባሮችን ሊያስተናግዱም ይችላሉ። ተንቀሳቃሽ የመማርያ ክፍሎች ከሌሎች የ MCPS መማርያ ክፍሎች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የጤና ደህንነት ደረጃ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

E. በስቴት የተመደበ የመያዝ አቅም (SRC) በሜሪላንድ ስቴት የሚገለጸው፥ ት/ቤት ሊቀበላቸው የሚችል የተማሪዎች ቁጥር ስቴት ባስቀመጠው የተማሪ ብዛት- ለ-ክፍል እና በትምህርት ቤት የማስተማሪያ ቦታዎች ብዛት መሆኑን ይገልጻል። የካፒታል ፕሮጀክቶችን የስቴት የባጀት አቅም ብቁነትን ለመወሰን ስቴት SRC ን ይጠቀማል። SRC የ CIP እና የማስተር ፕላን ተቀጥያ ሆነው ለት/ቤቶች ቀርበዋል።

F. የትምህርት ቤት ስፋት/መጠን ማለት እንደሚከተለው የትምህርት ፕሮግራምን በሙሉ ለማስተናገድ የሚያስፈልግ ያክል ኤከሬጅ ነው:-

1. የኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች — የቦታ/ሳይት መስፈርቶችን ጨምሮ የትምህርት ፕሮግራም የሚይዝ፣ ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችል 7.5 acres እንዲሆን ይመረጣል። የ 7.5 ኤከር መስፈርት የተመሠረተው ሁነኛ በሆነ ክፍት ቦታ ላይ ሲሆን፣ እናም መጠኑ እንደ ቦታዉ አቀማመጥ ቅርጽ፣ በዙሪያዉ ባሉት የቦታ እጥረቶች/ገደቦች ፣ በመልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ላይ ሊኖር የሚችል የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና እቅድ ውስጥ በሚካተቱት ነገሮች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

2. መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ሚድል ስኩል) — የትምህርት ፕሮግራም፣ እና የቦታ ስፋትን ጨምሮ ተግባር ላይ የሚውል 15.5 acres ቢሆን ይመረጣል። የ 15.5 ኤከር መስፈርት የሚመሠረተው ሁነኛ በሆነ ክፍት ቦታ

ላይ ሲሆን፣ እናም መጠኑ እንደ ቦታዉ አቀማመጥ ቅርጽ፣ በዙሪያዉ ባሉት የቦታ እጥረቶች/ ገደቦች፣ በመልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ላይ ሊኖር የሚችል የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና እቅድ ውስጥ በሚካተቱት ነገሮች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

3. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች — ለማስተማር ፕሮግራም የሚመጥን፣ የቦታ ስፋት መስፈርትን አካቶ ቢያንስ 35 acres ቢሆን ይመረጣል። የ 35 ኤከር መስፈርት የሚመሠረተው ሁነኛ በሆነ ክፍት ቦታ ላይ ሲሆን፣ እናም መጠኑ እንደ ቦታዉ ቅርጽ፣ በዙሪያዉ ባሉት የቦታ እጥረቶች/ገደቦች ፣በመልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ላይ ሊኖር የሚችል የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና እቅድ ውስጥ በሚካተቱት ነገሮች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

G. ቁልፍ የሆኑ የፋሲሊቲ አመላካቾች (KFI) ማለት የመማር እና የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ባህሪያት እንደ ደህንነት፣ ሠላም፣ እና የተደራሽነት መስፈርቶች፣ ውስጣዊ ድባብ፣ ለፕሮግራሙ የቦታው አመቺነት/ግንኙነት፣ የህንፃው ጥራት፣ እንዲሁም የመሠረተ ልማት እና የንብረት መረጃ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ ባህርያት ናቸው። በ 2018-2019 የትምህርት ዓመት MCPS በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ስለእያንዳንዱ ምክንያት መሠረታዊ ነገሮችን፣ እና KFI መረጃ/ዳታ ከማስቀመጡም በላይ በየወቅቱ እየተገመገመ ክለሳ ይደረጋል። እነዚህ ወቅታዊ መረጃዎች ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ።

## V. የክለስተር አስተያየቶች/CLUSTER COMMENTS

A. የክለስተር ተወካዮች ፋሲሊቲዎችን የሚመለከቱ ማናቸውንም ስጋቶች፣ ቅድሚያ ትኩረት የሚያሻቸውን ነገሮች፣ ወይም ለትምህርት ቤቶቻቸው አስፈላጊ የሆኑ አስተያየቶችን ከ PT(S)A አመራር፣ ከርእሰመምህራን፣ እና ከማህበረሰብ ጋር በመመካከር በየዓመቱ ጁን ላይ፣ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ያቀርባሉ።

B. ስለ ፋሲሊቲዎች ማሳደግ/ማሻሻል በ CIP ላይ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት አማካይነት በሚቀርቡ እቅዶች/ሪኮመንዴሽኖች ውስጥ ከክለስተር የሚቀርቡ አስተያየቶች ግምት ውስጥ ይገባሉ።

## VI. ስለ ፋሲሊቲ እቅድ የውሳኔ አሰጣጥ ማእቀፍ

A. በየዓመቱ፣ የአዳዲስ ተማሪዎች ምዝገባ ትንበያ ከተሠራ እና ሌሎች ከላይ የተገለጹ ዝርዝር ሁኔታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ፣ የክለስተር አስተያየቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የ MCPS ሥራ ባልደረቦች ስለፋሲሊቲ ለውጥ ፍላጎት በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ላይ እንደተገለጸው KFI ዘይቤ በመጠቀም አማራጮችን በቅደምተከተል ይለያሉ ስለትምህርት ፋሲሊት እቅድ/Educational Facilities Planning። ለፋሲሊቲ ፍላጎቶች እና የአቅም መስፈርቶች ምላሽ የመስጠት አማራጮች የሚያካትቱት—

1. ትምህርት ቤቶችን በተፈላጊው ጥሩ ሁኔታ ለማቆየት ጠቃሚ የሆኑ እና የጠቃሜታነታቸውን እድሜ ለማራዘም ለምሳሌ:- የሙቀት፣ የአየር መዘዋወር ማስተካከያ፣ የአየር ሙቀት/ቅዝቃዜ ሁኔታ ማስተካከል፣ እና መካኒካል ሲስተሞችን፣ ጣራዎችን፣ እና በርካታ ሌሎች የህንጻ እና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ካውንቲ-አቀፍ ሲስተም የመተካት ፕሮጀክቶች፣ እና

2. መጠኑን ለማሳደግ፣ እድሳት፣ ማስተካከያ፣ ለሌላ ዓላማ ማዘጋጀት፣ ወይም በአገልግሎት ላይ ያሉትን ፋሲሊቲዎች ለመተካት፣ ወይም ያሉትን እንደገና ለመጠቀም ወይም ያለውን ቦታ አሻሽሎ በሌላ ፋሲሊቲ እንደአስፈላጊነቱ የመጠቀም የተለየ ፋሲሊቲን የሚመለከቱ ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶች። እንደዚህ ዓይነት የፕሮጀክት አማራጮች አዲስ ፋሲሊቲ መገንባት ወይም ባለው ፋሲሊቲ ላይ ተጨማሪ ግንባታን ያካትታል።

B. ስለ ፋሲሊቲ ፍላጎት እና ተፈላጊ የአቅም ማሟላት አማራጮችን ምላሽ የመስጠት እንደዚሁ የሚያካትተው፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ የመቀበል/የምዝገባ አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ት/ቤቶችን ካፒታል በማያሻው ስትራተጂ/ስልት አቅምን ለማስተካከል እና/ወይም ከአቅም በላይ ከተጣበቡ ትምህርት ቤቶች ማዛወርን ማበረታታት፣ ነገር ግን በዚህ አያበቃም ለ—

1. የወሰን ለውጦች፣ ወይም

2. መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች (ኮንሶርሺያ የመሣሠሉት)፣ እና/ወይም

3. የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ጥምረት።

C. የውሳኔ አሰጣጥ ማእቀፍ ውስጥ በትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንዳት በተገለጸው መሠረት፣ የአርኪቴክት መረጣ፣ የፋሲሊቲው ዲዛይን/ንድፍ፣ እና ሌላ ከፋሲሊቲ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተጨማሪ ማካተት ያስፈልጋል።

VII. የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም

A. በየዓመቱ ፎል ላይ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ ዓመታዊ የካፒታል በጀት እና የስድስት-ዓመት CIP ወይም ቀደም ሲል የተወሰነውን CIP ማሻሻያዎችን አስተያየቶች/ሬኮመንዴሽኖችን ይፋ ያደርጋል።

B. በተጨማሪ፣ ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ወሰን/ድንበሮችን፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምደባ እቅዶች፣ የት/ቤት መዘጋት እና/ወይም ጥምረት፣ እና ማናቸውም ሌላ የፋሲሊቲ እቅድ አስተያየቶች/ሬኮመንዴሽንስ ማህበረሰቡ እንዲመለከተው ይበልጥ ጊዜ ስለሚያስፈልግ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

C. የስድስት-ዓመት CIP የሚከተለውን ያካትታል፡-

1. ለቦርድ ምልከታ/ግምገማ እና ትግበራ መደበኛ ስርአት፡-

a) ትምህርት ቤት ለመቀበል/ለማስገባት ተመራጭነት ያለው መጠን/ከዚህ እስከዚህ ተብሎ የሚወሰን

b) የፕሮግራሙ አቅም እና የፋሲሊት አጠቃቀም ስሌቶች/እሳቤዎች

c) የትምህርት ቤት የቦታ መጠን/ስፋት

2. ስለተማሪ አቀባበል ግምት አሠራር ዘዴ መነሻ

3. የወቅቱ የተማሪ ምዝገባ ቁጥር፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስብጥር መገለጫዎች፣ እና የፋሲሊት አጠቃቀም ሁኔታዎች/መገለጫዎች

4. የፕሮግራሙ አቅም እና የፋሲሊት አጠቃቀም ትንታኔ

5. አንደኛ ደረጃ(ኤለመንተሪ)፣ መካከለኛ (ሚድል)፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምዝገባ ትንበያዎች ለእያንዳንዱ የስድስት-ዓመት እና የረዥም-ጊዜ ትንበያዎች ለ10 እና 15 ዓመት የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

6. የድርጊት/የተግባር ምክረሃሳብ፣ የትምህርት ቤት አቅምን መቀየር/መለወጥ፣ አዳዲስ ፋሲሊቲዎች፣ ትላልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶች፣ የፕሮግራም ቦታዎች፣ እና/ወይም ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት።

7. ካውንቲ አቀፍ የመዋቅሩን ፕሮጀክቶች መርሃ ግብር በየፈርጁ፣ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ዋና/ትልልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶችን፣ እና በ CIP እና ማስተር ፕላን ምዕራፍ 1 ላይ እንደተገለጸው አዳዲስ ፋሲሊቲዎች።

8. በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት አማካይነት የካፒታል ባጀት ምደባ ይዘት ጠቅለል ያለ ሪኮመንዴሽን

D. በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ያስፈልጋሉ ተብለዉ ከታመኑ በጉዳዮች ላይ ተጨማሪ መረጃዎች ለማቅረብ ለ CIPው ማሟያዎች ሊገለፁ ይችላሉ

E. የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንደንት ያቀረቧቸው የ CIP ሃሳቦች/አስተያየቶች በ MCPS ድረገ-ገጽ ላይ ይወጣሉ። ለቦርድ አባላት እና ለቦርድ ሠራተኞች፣ ለ MCPS ሥራ አስፈጻሚ ሠራተኞች፣ እና የ MCCPTA ፕሬዚደንት፣

የክልል MCCPTA ምክትል ፕሬዚደንቶች እና የክለስተር አስተባባሪዎች የ CIP ሠነዶች ይቀርባሉ። በተጨማሪ፣ የCIP ህትመት እና መስመር ላይ መገኘት ማስታወቂያ ለርእሰመምህራን፣ የ PT(S)A ኣመራር፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ እና ለሲቪል ቡድኖች ይላካል። ይህ ማስታወቂያ የቦርዱን የስራ ክፍለጊዜዎች፣ ህዝባዊ ችሎቶች፣ እና CIP ላይ ተግባሬን ያካትታል።

F. በ CIP ላይ ለግምገማ እና ለእርምጃ በየአመቱ የቦርዱ የጊዜ ሰሌዳ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ክፍለ ጊዜዎችን እና ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ችሎቶችን ከኖቬምበር መጀመሪያ እስከ አጋማሽ ድረስ፣ እና ከኖቬምበር አጋማሽ እስከ ኖቬምበር መገባደጃ ድረስ ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል። (ስለ ህዝብ አስተያየት ሂደት ሰክሽን/Section XI.B እና ስለ አመታዊ ካለንደር ሰክሽን Section XII ይመልከቱ።)

G. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ስለ CIP ማናቸውም የተለየ የእቅድ ጉዳዮች እና/ወይም ማሻሻያዎችን ምክረ ጉዳይ/ሬኮመንዴሽን ፌብሩወሪ አጋማሽ ላይ ይዘጋጃሉ። ስለ እነዚህ ጉዳዮች የቦርዱ የጊዜ ቅደምተከተል አንድ ወይም የበለጠ የሥራ ክፍለጊዜዎችን እና ፌብሩወሪ/ማርች ላይ አንድ ወይም የበለጠ የማህበረሰብ ውይይቶችን እና ኤፕሪል ላይ ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል። አስፈላጊ ከሆነ፣ በእቅድ የተለዩ ጉዳዮች የጊዜ ቅደምተከተልን በሚመለከት በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሂደት በቂ ጊዜ ለመስጠት እንዲሙች ይሻሻላል።

H. ያልተለመዱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ቦርዱ በሚያረጋግጥበት ወቅት፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ CIP ምክረ ጉዳዮችን/ሪኮመንዴሽን ለማድረግ፣ ስለፋሲሊቲ እቅድ ስራዎች፣ ስለቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ድንበር/ክልሎች፣ መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅዶች፣ ወይም ትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት አማራጭ የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል።

I. ቦርዱ ገምግሞ እርምጃ ከወሰደ በኋላ፣ ቦርዱ የሚጠይቀው CIP፣ በጠቅላላ የተጠየቁት የካፒታል ፕሮጀክቶች መግለጫ ቅጾችን ጭምር (PDFs)፣ እንዲመለከቱትን እና እንዲጸድቅ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል/ምክር ቤት (County Council) እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ሥራ አስፈጻሚ ይቀርባል። ቦርዱ የሚጠይቀው CIP ለመረጃ ወደ M-NCPPC ይላካል።

J. የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ ሃሳቦች በአጠቃላይ የካውንቲ ካውንስል CIP ውስጥ እንዲካተቱ ጃንዋሪ 15 ለካውንቲ ምክር ቤት ይላካሉ። የካውንቲው ምክር ቤት በቦርድ-በተጠየቀው CIP ለግምገማና ለውሳኔ እርምጃ የጊዜ መስመር ከፌብሩወሪ እስከ ሜይ ድረስ ነው።

K. ሜይ መገባደጃ ላይ የካውንቲው ካውንስል በየሁለት ዓመት የሚዘጋጅ የስድስት-ዓመት CIP ማሻሻያዎችን ይወስናል።

## VIII. የትምህርት ፋሲሊቲዎች ማስተር ፕላን (MASTER PLAN)

A. በየዓመቱ ጁላይ ላይ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ አቅም መስፈርቶች እና አስፈላጊ ፋሲሊቲዎችን የካውንቲ ምክር ቤት/ካውንስል ያፀደቃቸውን የካፒታል እና ቦርድ ያፀደቃቸው ሌሎች ካፒታል ያልሆኑ ስትራቴጂዎችን ጠቅላላ አጭር ዘገባ ይፋ ያደርጋል። በስቴት የህዝብ ትምህርት ቤት ግንባታ ፕሮግራም ህግ - እና ደምብ መሠረት፣ ይህ ሠነድ፣ ማስተር ፕላን ያስፈልጋል።

1. ማስተር ፕላኑ በካፒታል ፕሮጀክቶች ላይ ለተገመተው ተጽእኖ በካውንቲው ምክር ቤት የተፈቀደውን የገንዘብ ድጋፍ እና ለተፈላጊ የአቅም መስፈርቶች እና ለፋሲሊቲ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት በቦርድ የፀደቁትን ማናቸውንም የካፒታል ያልሆኑ ስትራቴጂዎችን ያካትታል።

2. ከ CIP በተመሣሣይ፣ ማስተር ፕላኑ የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) የሚከተሉት መመዘኛዎች፡-

(1) ተመራጭ የት/ቤት ምዝገባዎች መጠን

(2) የፕሮግራም የማስተናገድ አቅም/ስፋትና የመገልገያ ኣጠቃቀም ስሌቶች

(3) የትምህርት ቤት ሰፈር/ቦታ ስፋት

b) ለመቀበያ/ምዝገባ ግምት የአሠራር ዘዴ ዳራ/መነሻ ምክንያቶች መረጃ

c) የወቅቱ የተማሪ ምዝገባ ቁጥሮች፣ የትምህርት ቤት ስብጥር አጭር ታሪክ፣ እና የፋሲሊቲ አጭር ታሪክ

d) የፕሮግራም የማስተናገድ አቅም/ስፋትና የመገልገያ ኣጠቃቀም ስሌቶች

e) አንደኛ ደረጃ (ኤለመንተሪ)፣ መካከለኛ ደረጃ፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምዝገባ/መቀበያ ትንበያ ለእያንዳንዱ የስድስት-ዓመት እና የረዥም-ጊዜ ትንበያዎችን ለ10ኛ እና 15ኛ ዓመት ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች። ይህ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ቀደም ባለዉ ፎል ላይ የተደረገዉን ትንበያ ከአንድ-ዓመት የስፐሪንግ ትንበያ ጋር፣ እና በድንበር ለውጦች፣ ጂኦግራፊያዊ በተማሪ ምርጫ የምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ጥምረቶችን፣ ወይም ቦርድ በደነገገው ሌሎች ለውጦች ሳቢያ የሚከሰቱ ማናቸውንም የምዝገባ/የመቀበል ትንበያ ለውጦችን ያንፀባርቃል

f) በካውንቲ ምክር ቤት-የፀደቁ PDF ለሁሉም ካፒታል ፕሮጀክቶች ከፕሮግራሞች፣ የተገመቱ ዋጋዎች፣ እና የገንዘብ ምንጮች፡-

IX. የረዥም ጊዜ እቅድ

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የረዥም-ጊዜ (ይህም ማለት፡- ከስድስት-ዓመት የዘለለ የ CIP ጣልቃ ገብ) ስለ CIP ዝግጅት የማሳወቅ እቅድ ማእቀፍ MCPS ወደፊት እንዲያስብበት እና በፔዳጎጂ ከዳበሩ የፋሲሊቲ አማራጫች እና ለትምህርት ፕሮግራሞች የፈጠራ አቀራረብ፣ እንዲሁም የክፍል መጠን ለውጦች፣ ከመደበኛ ቦታዎችን የተለዩ ቦታዎችን ስለመጠቀም፣ እና ሌሎች ተስማሚ አቀራረቦችን ይጠቀማል።

B. እነዚህ የረዥም-ጊዜ ሁኔታዎች እቅድ ማእቀፍ በሪጅናል ወይም በክለስተር ደረጃ፣ አራት የእድገት ማኔጅመንት ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የፋሲሊቲ እቅድ ተፅእኖን ይዳስሳሉ፡-

1. ከፍተኛ የምዝገባ እድገት

2. መካከለኛ/ዝቅተኛ የምዝገባ እድገት

3. የምዝገባ እድገት የለም

4. ምዝገባ እየቀነሰ ነው

C. አንድ ትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤቶች ምን ያህል ወይም ለወደፊት ከልክ ያለፈ አጠቃቀም ወይም አነስተኛ ጥቅም ላይ እንደሚውል ስለማንኛውም ሁኔታ ትንታኔው ይወስናል። ከእነዚህ ትንታኔዎች የሚመነጩት አማራጮች በአንፃሩ በዚህ ሳይወሰን፣ የሚከተለውን የረዥም-ጊዜ አቀራረብ ይጠቁማሉ፡-

1. ስለ አገልግሎት አሰጣጥ ለውጦች፣ ቦታ፣ ወይም የፕሮግራሞች ቁጥር፣ የምዝገባ ሁኔታ እና የክፍል መጠን፣ የክፍል አደረጃጀት፣ ወይም ዋና/ቁልፍ የጊዜ ሠሌዳዎች

2. ስለ አካላዊ የአቅም ማሳደግ (ተጨማሪ)

3. መደበኛ ያልሆኑ ቦታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ወይም ያሉትን ስፍራዎች መደበኛ ያልሆነ አጠቃቀም

D. ስለ ረዥም ጊዜ የፋሲሊቲ ዕቅድ ጉዳዮች እና ስትራቴጂዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰብ ያለውን የበለፀገ ልምድ እና እውቀት ላይ በመመርኮዝ ከስድስት-ዓመት ያለፈ የ CIP የጊዜ ማዕቀፍ ነገር ግን ከ 10 - 15 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የጊዜ ማእቀፍ የሚያስፈልጋቸውን ባለብዙ ፈርጅ የትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች እና እቅድ በሚገናኙ ጉዳዮች የማህበረሰቡን ራዕይ በሚመለከት ስለ ትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች እና እቅድ MCPS ን ለማማከር የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የፋሲሊቲዎች አማካሪ ኮሚቴ አቋቁሟል። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ግባት ጋር የፋሲሊቲ አማካሪ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል።

X. ስለተጠቀሱት ፋሲሊቲዎች ጉዳይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሂደት መመሪያ

A. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መመሪያ

1. በተለይም ስለ ሚከተለው የ MCPS ፋሲሊቲ-ጋር የተገናኘ እቅድ ሂደት መሣካት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝነት አለው፡-

a) ለአዲስ ትምህርት ቤቶች የቦታ መረጣ

b) የትምህርት ቤት ክልሎች/ድንበር

c) መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች

d) የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት

e) የፋሲሊቲ ዲዛይን

f) በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የተለዩ ሌሎች ከፋሲሊቲ ጋር - የተገናኙ ጉዳዮች

2. ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ABA የሚጣጣም፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ/Community Involvement፣ እና የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA፣ ስለ ትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning፣ በሰክሽን/Section V.A.1 የተገለጸውን ለማስኬድ በሠራተኞች የተዘጋጀው ከፋሲሊቲ ጋር የተገናኙ አማራጮች በማህበረሰቡ ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እንደሚኖራቸው ሱፐርኢንተንደንቱን ለማማከር MCPS የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ይፈልጋል።

a) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ግብአቶችን ለመስጠት እና ቀጥታ ሥራተኝነት ያሉትን እድሎች ስለመፈለግ – ይፋ ያደርጋል

(1) የበርካታ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ

(2) የሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ሰፊ ውክልና፣ እና

(3) የተለያዩ በርካታ አመለካከቶች

b) በእቅድ ሂደት ላይ የቅድሚያ ባለድርሻ አካላት ሁኔታው የሚነካቸው/የሚመለከታቸው ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ሠራተኞች፣ እና ተማሪዎች ናቸው። ከ MCCPTA፣ የአካባቢ PT(S)As፣ ወይም ሌላ ወላጅ/ሞግዚት ወይም የተማሪ ቡድኖች፣ ከ MCPS የሥራ ተወካዮች ጋር፣ የሚመለከታቸው ማዘጋጃ ቤቶች/የከተማ አስተዳደር፣ የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር ኤጀንሲዎች፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ እና ሌላ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች፣ እንደየአግባብነቱ ተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ይካተታሉ።

c) የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጎልበት ሠራተኞች በርካታ የተደራሽነት ስልቶችን/ስትራቴጂዎችን

ይተገበራሉ።

(1) ባለድርሻ አካላትን የማሳተፍ ስልት እንደሂደቱ ተፈጥሮ፣ መጠን፣ እና ስፋት እንደአግባቡ ሊለያይ ይችላል።

(2) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፡- በዚህ አያበቃም፣ ሥርአት አቀፍ ኮሚቴዎችን ወይም አማካሪ ቡድኖችን፣ የትኩረት ቡድኖች፣ የሥራ ግብረኃይል፣ የሥራ ቡድኖች፣ የክብ ጠረጴዛ ውይይት ቡድኖች፣ ዳሰሳዎችን፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግንኙነቶች፣ እና/ወይም ሌላ የህዝብ የእቅድ ዝግጅት ክፍለጊዜዎች፣ እንደ ቻርት የመሣሠሉ ፍላጎት ባላቸው መካከል ስለሚደረጉ ትብብሮች ዲዛይን የተደረጉ ወይም ስለሚመለካተቸው ክፍሎች እና ለሠራተኞች መረጃ እና ግብረመልስ የሚሰጡ ነገሮችን ያካትታል።

(3) በማናቸውም ጊዜ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኞች የዳሰሳ ጥናት፣ ወይም በቴክኖሎጂ የሚታገዝ ግንኙነት ወይም በሌላ ዘዴ ህዝባዊ መድረክ እንዲጠቀሙ መመሪያ ይሰጣል።

B. ስለ ትምህርት ቤቶች ድንበር/ወሰን እና ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ አማራጭ እቅዶችን ስለማዳበር ተጨማሪ መመሪያዎች

1. ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉበት የተለዩ አማራጮች ከመቅረባቸው አስቀድሞ፣ ስለ ትምህርት ቤት ወሰን/ክልሎች ለውጥ እና/ወይም በአካባቢው ስነምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት በውንቲው ተፅእኖ የሚኖረው ጂኦግራፊያዊ የሆነ በተማሪ ምርጫ የሚደረግ ምደባ እቅዶችን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለቦርድ ሪኮመንዴሽን ያቀርባል።

2. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በርካታ ደረጃዎች ያሉት በመጀመሪያ ደረጃ መከናወን ያለባቸውን ዝርዝሮች ትንተና በማድረግ ቅድሚያ መሰጠት ያለበትን በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ላይ የተገለጹትን አራት ምክንያቶችን ያገናዘበ አፋጣኝ ምላሽ መሰጠት ያለበትን ከአነስተኛው ክፍል ያቀርባል፣ ከዚያም በስነምድራዊ አቀማመጥ ያሉ አካባቢ(ዎች) ሙሉ በሙሉ በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ላይ የተገለጹትን አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ከፍተኛውን ደረጃ በርካታ ደረጃዎች ያሉት ሪኮመንዴሽኖችን ያዘጋጃል ስለ ትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning

በተለይም፣ በትምህርት ቤት የመቀበል አቅም ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ውስንነት እንደሚኖረው የተገመተ የካፒታል ፕሮጀክት (ለምሳሌ፡- የትምህርት ቤቱን አቅም ከ20 ፐርሰንት ባነሰ የሚጨምር ወይም የመግሪያ አካባቢ ላይ መጠነኛ ለውጥ ብቻ የሚያደርግ) ሪኮመንዴሽን ምላሽ ለመስጠት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የትምህርት ቤት ድንበር፣ ወሰን፣ ክልል መጠን እና/ወይም መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የሆነ በተማሪ ምርጫ የመመደብ እቅድ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን ክለስተር ብቻ እና ከክለስተሩ ውጪ በአቅራቢያ የሚያዋስኑ ትምህርት ቤቶች ላይ ተጽእኖ በሚደረግ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል።

a) በሰፊው ማህበረሰብ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሣድር የሚታመንበት አስፈላጊ ጉዳይ የአጎራባች ክለስተሮችን ማህበረሰቦች ተሳትፎ ማስፋት አማራጭ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

3. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ፋሲሊቲ-ጋር የተገናኙ ጥረቶችን በተመለከተ ለቦርድ ሪኮመንዴሽን ከማቅረቡ አስቀድሞ በእርግጠኝነት ተጽእኖ የደረሰባቸውን ማህበረሰቦች ይለያል።

4. የትምህርት ቤትን ክልል እና/ወይም ትኩረት የተሰጣቸው የመልከአምድራዊ አቀማመጥ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅዶችን ቦርዱ አንድ ጊዜ ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፉ በፖሊሲ/Policy FAA ላይ በተገለጹት አራት ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ በርካታ አማራጮችን ያዘጋጃሉ፣ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning እና እያንዳንዱ አማራጭ እነዚህን ሊያራምዱ የሚችሉበትን ምክንያታዊነት መግለጫ ይሰጣል፡-

a) የተማሪ ማህበረሰብ ስብጥር ባህርይ

የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ተከትሎ፣ የትምህርት ፋሲሊቲ እቅድ/Educational Facilities Planning፣ የአማራጭ ትንታኔዎች በአጠቃላይ በተጎዱት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አማራጮች ተፅዕኖ ከግምት ዉስጥ ያስገባሉ።አማራጮቹ በእያንዳንዳቸው የሚመለከታቸውን ትምህርት ቤቶች ብዝሃነትን ያቀፈ የተማሪ አካል ለመፍጠር ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACD ጋር የማጣጣም ጥረት ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው ከጥራት ጋር የተዋሃደ ትምህርት/Quality Integrated Education። ይህ ማለት በሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች ስነህዝብ ስብጥር እና የአካባቢ መልከአምድራዊ አቀማመጥ መካከል ያለው የጎላ ልዩነት በማናቸውም ሌላ ምክንያት ሊረጋገጥ የማይችል ቁልፍ ምክንያት ይሆናል። ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የተለያዩ አማራጮችን የሚያመለክት የስብጥር መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፡- የተማሪው ህብረተሰብ የዘር/የጎሣ ስብጥር፣ የተማሪው ሕብረተሰብ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ስብጥር፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ደረጃ፣ እና ሌላ አሳማኝ የስነህዝብ ስብጥር አመላካች ነገሮች እና በተለዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ያለው ተሳትፎ። አማራጮቹ በእነዚህ ክፍሎች ስለ ስብጥር በተጠቀሱት መረጃዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግምት መሰጠት አለበት።

b) ጂኦግራፊ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ቤቶች የማህበረሰብን ተሳትፎ ለማጎልበት ከሚሰጠው ትኩረት አንፃር አማራጮቹ፡- የግዴታ ካልሆነ በስተቀር፣ ማህበረሰቡ ለትምህርት ቤቶች ያሏቸውን መልከአምድራዊ አጎራባችነት፣ ርቱእነት፣ የትራፊክ ፍሰት፣ የመጓጓዣ ሁኔታዎችን (የህዝብ አቋራጭ መተላለፊያን ጨምሮ)፣ እና የመሬት አቀማመጥን ማጤን አለባቸው። የዚህ ትንታኔ አካል እንደመሆኑ፣ ወደ ትምህርት ቤት የእግር ጉዞ እና ለመጓጓዣ ያለው ርቀት መታየት አለበት። በተጨማሪ፣ አማራጮቹ  በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክልል/ክለስተር ያሉትን ብቻ ሳይሆን ቢያንስ ከክልል ውጭ በአዋሳኝ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

c) የትምህርት ቤት ምደባዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ

የአማራጮቹ ምደባዎች በተቻለ መጠን ለረዥም ጊዜ ዘለቄታ ያላቸው ውጤት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። እነዚያኑ ተመሣሣይ ተማሪዎች የሚመለከት ተማሪዎችን እንደገና ምደባ ሲደረግ በቅርብ የተደረገ የወሰን-ድንበር ወይም ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅድ ለውጦችን፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት መዝጋት እና መጣመር ትኩረት መሰጠት አለበት።

d) የፋሲሊቲ አጠቃቀም

የት/ቤት ክልል/ወሰን እና መለከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች በፋሲሊቲ ኣጠቃቀሞች በተቻለ መጠን በረዥም ጊዜ ከ80 በመቶ እስከ 100 በመቶ የብቃት ክልል ውስጥ መገኘት ኣለባቸው። በማህበረሰቡ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ፋሲሊቲን ከአንድ ክላስተር በላይ በጋራ የመጠቀም ፕላን በአንዳንድ ሁኔታዎች በጣም ውጤታማ ፕላን ሊሆን ይችላል። እቅዶቹ በተቻለ መጠን የካፒታል እና የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለመቆጠብ የሚያስችል ኃላፊነት የተሞላበት መሆን አለበት።

5. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በሚጠናቀቅበት ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ስለተጠቀሙበት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሂደት፣ ሠራተኞች ያዘጋጇቸው አማራጮች፣ እና የባለድርሻ አካላት ግብረመልስን የሚያካትት ነገር ግን በዚህ ያልተገደበ አጭር መግለጫ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርብ ሪፖርት ያዘጋጃሉ።

6. በተጨማሪ፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ማናቸውንም የተናጠል PT(S)A መደብ/አመለካከት ወረቀቶችን ለመቀበል ይችላል።

7. ለቦርዱ ሬኮመንዴሽኖች በሚዘጋጁበት ወቅት፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሪኮመንድ ስለተደረጉት ስለ እያንዳንዳቸው ሰክሽን/Section X.B.2 እና X.B.4. ላይ በተገለጸው መሠረት የሚታይ እና ምክንያታዊ የሆነ

ውጤት እንደሚያመጣ አመክንዮ ይሰጣል። እያንዳንዳቸው ምክንያቶች ታሳቢ ቢደረጉም፣ እያንዳንዱን/ሁሉንም የቀረቡትን አስተያየቶች ከእያንዳንዱ/ሁሉም ምክንያቶች ጋር ለማገናዘብ አይቻልም ይሆናል።

8. ይህ መመሪያ እንደዚሁ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተለይተው የሚቀርቡ ለሌሎች ከፋሲሊቲ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል።

C. አዲስ የትምህርት ቤት ቦታ አማራጮችን ስለማጎልበት ተጨማሪ መመሪያዎች

በቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የሚከተሉት ምክንያቶች ተገናዝበዋል/ታሳቢ ተደርገዋል፣ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning፣ በስጦታ ወይም በግዢ የተገኙ እና በቦርድ ኢንቬንቶሪ ላይ የተመዘገቡ አዲስ የትምህርት ቤት ቦታዎችን ጨምሮ በሚገመገሙበት ጊዜ፣

1. መልከአምድራዊ/ጂዮግራፊያዊ ስፍራ ከነባር ወይም የወደፊት የተማሪ ህዝቦችና ነባር ትምህርት ቤቶች ሲዛመድ

2. ስፋት በኤከር ሲለካ

3. የመሬት አቀማመጥ እና ሌሎች አካባቢያዊ ጠባዮች

4. የመገልገያዎች (ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ወዘተ) መገኘት/መኖር

5. ፊዚካል/አካላዊ ሁኔታ

6. የቦታ መኖር እና ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ

7. የማግኘት ዋጋ የግል ንብረት ከሆነ

D. የፋሲሊቲ ዲዛይን/ንድፍ

የትምህርት ፋሲሊቲ ዲዛይኖች በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ መርህ እና በወቅቱ የትምህርት ፕሮግራም ፍላጎት፣ እንዲሁም ለወደፊት ታሳቢ በተደረገ የፕሮግራም ፍላጎት መሠረት ጤናማ እና ሰላማዊ አካባቢን መፍጠር አለባቸው። የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚያስፈልገው አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት በሚያመራ ሂደት ወይም እንደሚከተለው በነባር ህንፃዎች ላይ የሚደረግ ተጨማሪ ግንባታ ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ነው፦

1. የትምህርት ዝርዝሮች የሚገልጹት የማስተማር ፕሮግራምን ለመደገፍ ምን ያህል ቦታ እንደሚያስፈልግና ስለህንጻው አቀማመጥ እና ዲዛይን የንድፍ ባለሙያን ይመራል። ስለተዘጋጁት ፕሮጀክቶች ትምህርታዊ ዝርዝሮች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የካፒታል እቅድ ሠራተኞች ከትምህርት ፕሮግራም ሠራተኞች እና ከሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች ርእሰመምህራን እና ሠራተኞች ጋር በመቀናጀት ይዘጋጃል።

2. የዲዛይን አማራጮች የሚቀረጹት ትምርታዊ ዝርዝሮችን በመገምገም የመጀመሪያ ዲዛይን ለመስራት በተመረጠ አርቲኬት(ቶች) አማካይነት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከዚህ እንደሚከተለው ተሰባስቧል፦

    a) ስለ ካፒታል ፕሮጀክቶች ዲዛይን የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማግኘት/ለማጎልበት የ MCPS ሠራተኞች የተለያየ አይነት ሰፊ በርካታ ስትራቴጂዎችን ይተገብራሉ።

    b) የማህበረሰብ ቡድኖች ተወካዮች፣ የከተማ አስተዳደር፣ የካውንቲ የመንግስት አስተዳደር (የሞንትጎመሪ ካውንቲ የፕላን መምሪያ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፓርኮች መምሪያ)፣ እና አዋሳኝ የንብረት ባለቤቶች፣ ካሉ፣ ለአዲስ ትምህርት ቤት ሥራ ዲዛይን ሥራ በሚዘጋጅበት ወቅት እና በነባር ህንፃ ላይ ለሚጨመር ዲዛይን ወይም ለነባር ትምህርት ቤቶች ትልልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዲዛይን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

3. የመጀመሪያውን ዲዛይን/ንድፍ ያካተተ፣ የመጀመሪያው እቅድ እንዲፀድቅ ለቦርድ ይቀርባል።

E. የትምህርት ቤት መዘጋት ወይም ጥምረቶች

ከላይ ክፍል X.B.4 ላይ ከተገለጹት ምክንያቶች በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤት መዝጋት እና ማጣመር ሲያስፈልግ ስለ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሜሪላንድ ህግ መስፈርቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

XI. ከትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት በሚቀርቡ ሪኮመንዴሽኖች ላይ የሚወሰድ የቦርድ ተግባር

A. ከላይ ክፍል VII ላይ እንደተገለጸው ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርቡትን አስተያየቶች ለመገምገም ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የሥራ ክፍለጊዜዎችን ይመድባል።

1. ስለ ቦታ መረጣ፣ ስለ ትምህርት ቤት ክልሎች መለከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ወይም ትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም የትምህርት ቤቶች ጥምረት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማራጭ ሃሳቦችን እንዲያቀርብ ቦርዱ በአብላጫ ድምፅ መጠየቅ አለበት።

2. በትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የውሳኔ ሃሳብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ትርጉም ያዘለ ማሻሻያ በቦርዱ አባላት በብዛት የሚደገፍ ኣማራጭ ያስፈልገዋል። በትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የውሳኔ ሃሳብ ቀደም ብሎ ያልተካተተ በማንም ወይም በኣንድ ትምህርት ቤት ማህበረሰብ በሞላ ተፅእኖ የሚያደርግ ማንኛውም ማሻሻያ ትርጉም ያዘለ ማሻሻያ ተብሎ መታሰብ ኣለበት። በቦርድ የሚቀርቡ አማራጮች በቦርድ ፖሊሲ/Section G of Board Policy FAA ላይ ከተገለጹት ምክንያቶች አንዱን ወይም የሚበልጠውን ያስፈጽማል የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ/Educational Facilities Planning።

3. የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የውሳኔ ሃሳቦች እና በቦርድ-የሚጠየቁ ኣማራጮች በቦርዱ የመጨረሻ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ለማህበረሰብ ትችት መቅረብ ኣለባቸው። በማንኛውም የስራ ክፍለጊዜ ኣንድ ኣማራጭ በቦርዱ ከተለየ፣ በኣማራጩ የህዝብ ኣስተያየትን መቀበል እንዲቻል ከዚያ ክፍለጊዜ በማከታተል ህዝባዊ ችሎት መካሄድ ኣለበት።

ይህ ትግባሬ የህዝብ ኣስተያየት ባገኘ ፕላን ላይ ትርጉም ያዘለ ተፅእኖ የማያደርግ ከሆነ በትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የውሳኔ ሃሳብ ወይም በቦርድ-በተጠየቀ/ቁ ኣማራጭ/አማራጮች ቦርዱ መጠነኛ ማሻሺያዎች የማድረግ ነፃነት ኣለው። ያለ በቂ ማስታወቂያ እና በሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ለኣስተያየት እድል ሳይኖር ኣማራጮች ከቦርድ የስራ ክፍለጊዜ በኋላ ግንዛቤ ኣይደረግባቸውም።

C. የቦርድ የህዝብ አስተያየት መቀበያ ሂደት

1. የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንዳንትን የ CIP አስተያየቶችን/ሪኮመንዴሽኖች ተከትሎ በየዓመቱ የህዝብ አስተያየት መቀበያ ሁነቶች ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ስለ ቦታ መምረጥ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የሆነ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ወይም የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረቶችን በሚመለከት እርምጃዎች ከመወሰዳቸው አስቀድሞ የህዝብ አስተያየት ውይይቶች ይካሄዳሉ።

a) የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የሚያቀርቡትን የካፒታል ባጀት እና የስድስት - ዓመት CIP ይፋ ከተደረገ በኋላ በመቀጠል የህዝብ አስተያየት መስሚ ሸንጎ ኖቬምበር ላይ ይደረጋል።

b) ቀደም ሲል ለህዝብ ይፋ ያልተደረጉ የሱፐርኢንተንደንት አስተያየቶች ካሉ ፌብሩወሪ መገባደጃ ወይም ማርች ላይ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ሸንጎ ሊካሄድ ይችላል።

c) ያልተለመዱ ሁኔታዎች መከሰታቸውን ቦርዱ ካመነበት እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት የተለየ እና/ወይም ሪኮመንዴሽኖችን ለማቅረብ ያጠረ መርሃ ግብር ያዘጋጀ እንደሆነ በአመቱ ውስጥ በሌሎችም ጊዜያት የህብረተሰብ ውይይቶች ይካሄዳሉ።

2. ከሌሎች የተሳትፎ መንገዶች በተጨማሪ፣ የማህበረሰብ አባላት ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ለቦርድ በጽሑፍ በሚደረጉ ግንኙነቶች፣ የህዝብ አስተያየቶችን፣ እና የህዝብ ምስክርነቶችን አስተዋጽኦ የማድረግ እድሎች አሏቸው።

3. የከተማ አመራር ቡድኖች፣ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ እና በህዝብ የተመረጡ ሃላፊዎች በህዝብ አስተያየት ሸንጎ ላይ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ።

4. MCCPTA ክለስተር አስተባባሪዎች፣ ከአካባቢ PT(S)A ፕሬዚደንቶች ጋር በማማከር፣ በማህበረሰብ ውይይት ላይ በክለስተር የታቀፉ ትምህርት ቤቶችን በመወከል ምስክርነቶችን እንዲያስተባብሩ እና የምስክርነት መርሃ ግብር ሲያዘጋጁ የተለያዩ አይነት ሃሳቦች እንዲቀርቡ ይበረታታሉ። የምስክርነት ወቅት ለያንዳንዱ ክላስተር ፕሮግራም የሚደረገውና የሚደራጀው በተቻለ መጠን በ PT(S)A ድርጅታዊ አሃዶች ("quad-clusters") እና/ወይም በኮንሶርሽም ነው።

5. የፅሁፍ አስተያየቶች ከማህበረሰቡ በማንኛውም ወቅት ተቀባይነት ያገኛሉ ነገር ግን፣ ሀሳቤ ውስጥ እንዲገቡ፣ ኣስተያየቶች ትግባሬ በቦርዱ ፕሮግራም ከመደረጉ በፊት ቢያንስ ከ48 ሰአቶች በፊት ቦርዱ ጋ መድረስ ኣለባቸው።

6. በማህበረሰብ ሸንጎዎች ላይ ለመናገር/ምስክርነት ለመስጠት ለሚፈልጉት የጊዜ ሠሌዳ ለማዘጋጀት የቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊነት አለበት።

    a) እንደተገለጸው በትምህርት ቦርድ የመመሪያ ሠነድ ላይ/Board of Education Handbook፣ ለ CIP ውይይቶች፣ ተማሪዎች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ እና MCCPTA በቅድሚያ አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ በመቀጠልም PT(S)፣ እና ከዚያ በኋላ እንደየአመጣጥ ቅደምተከተል ግለሰቦች እና የከተማ ዜጎች፣ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች ይሆናሉ።

    b) በህዝብ የተመረጡ ኃላፊዎች በአጀንዳዉ ላይ ለመናገር ራሳቸው የሚመርጡት ሠዓት ይመደብላቸዋል።

    c) በቦርዱ የሃሳብ አሰጣጥ ማስገንዘቢያ ላይ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ድርጅቶች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ እና ተመራጭ ኃላፊዎች ለቦርድ የሚያቀርቡት ሃሳብ በአምስት ደቂቃዎች ይወሰናሉ።

**XII.** ካለንዳር

የፋሲሊቲ እቅድ ሂደት በሞንትጎመሪ ካውንቲ በየሁለት ዓመት የ CIP ሂደት መሰረት የሚከናወን እና በዓላትን እና ሌሎች ያልተለመዱ ሁኔታዎችን ለማካተት የሚከተለዉን ካላንደር በመጠበቅ በየዓመቱ ማስተካከያዎች ይደረግበታል።

| | |
|---|---|
| የ MCPS የሥራ ባልደረቦች ስለፀደቀው CIP መረጃዎች ለመለዋወጥ እና ስለሚመጣው CIP ወይም የ CIP ማሻሻያ ጉዳዮችን ለማገናዘብ ከ MCCPTA፣ የአካባቢ ምክትል ፕሬዚደንቶች፣ የክላስተር አስተባባሪዎች፣ እና የ PT(S)A ተወካዮች ጋር ይገናኛሉ። | ሰመር |
| ለአዲሱ የ CIP ዑደት እዳ የመክፈል አቅም ላይ በመመርኮዝ ወጪ የሚደረግበትን አቅም በካውንቲው ካውንስል መመሪያ ይወሰናል። | የባለንደሎ ቁጥር የበጀት ዓመታት የኦክቶበር-መባቻ |
| የ MCPS የሥራ ባልደረቦች የምዝገባ አቅጣጫዎችን የፕላን ዝግጅት ጉዳዮችን ለቦርዱ ያቀርባሉ። | ፎል |
| ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ማካለል፣ መለከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ ጋር የሚገናኙ የበለጠ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው የህዝብ ምልከታን የሚሹ ጉዳዮችን የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት አዘጋጅቶ ሪኮመንዴሽኖችን ለቦርድ ያቀርባል። | ፎል |
| የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ዓመታዊ የካፒታል ባጀት እና የስድስት-ዓመት CIP ወይም የ CIP ማሻሻያዎችን በማዘጋጀት አስተያየቶችን ለቦርድ ያቀርባል። ከዚህ አቅርቦት ጋር በማያያዝ የቦርድ ኣባሎች ኣማራጮች ሊያቀርቡ የሚችሉበት ኣንድ የስራ ክፍለጊዜ ቦርዱ ሊያካሂድ ይችላል። | ፎል |
| ስለ CIP ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የስራ ክፍለጊዜዎችን በማካሄድ ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ በመለከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በሚመለከት ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቀረቡት ሪኮመንድሽኖች ላይ ሌሎች አማራጮችን ያገናዝባል። | ከኖቬምበር መግቢያ እስከ ኖቬምበር አጋማሽ |
| ስለ CIP ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ በመልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በሚመለከት በቀረቡት ሪኮመንድሽኖች ላይ ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የህዝብ ስብሰባ/ክፍለጊዜዎችን ያካሄዳል። በማንኛውም የስራ ክፍለጊዜ ኣንድ ኣማራጭ በቦርዱ ከተለየ፣ በአማራጩ የህዝብ ኣስተያየትን መቀበል እንዲቻል ከዚያ ክፍለጊዜ በማከታተል የህዝባዊ አስተያየት የመቀበያ ጊዜ መካሄድ ኣለበት። | ኖቬምበር አጋማሽ |
| ስለ ካፒታል ባጀት፣ CIP፣ ማሻሻያዎች፣ እና ማናቸውም የቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት፣ ወይም ሌላ ፋሲሊቲ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት ቦርዱ እርምጃ ይወስዳል። | ከኖቬምበር አጋማሽ እስከ ኖቬምበር መገባደጃ |
| የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ እና የካውንቲው ካውንስል ከቦርድ የቀረበለትን የካፒታል ባጀት እና CIP ተቀብሎ ይገመግማል። | ዲሰምበር 1 |
| የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ የቀረበለትን የካፒታል ባጀት እና CIP ወይም ማሻሻያዎችን ለካውንስሉ ያስተላልፋል። | ጃንዋሪ 15 |
| የካውንቲው ካውንስል ስለ CIP የህዝብ አስተያየቶችን ያዳምጣል። | ፌብሩወሪ - ማርች |
| የካውንቲ ካውንስል ከቦርድ የቀረበለትን እና የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ አስተያየት የተሰጠበትን የካፒታል ባጀት እና CIP ይመለከታል። | ማርች - ኤፐረል |
| በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንት የሚዘጋጁ ማናቸውም የሚተላለፉ የእቅድ ጉዳዮች፣ የቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ጥምረት፣ እና ሌላ ፋሲሊቲ ነክ ጉዳዮችን እና/ወይም የ CIP ማሻሻያ(ዎች) አስፈላጊ ከሆነ ቦርድ እንዲመለከታቸው ይፋ ይደረጋል። | ፌብሩወሪ- አጋማሽ* |
| ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊት ጋር ስለሚገናኙ ጉዳዮች በቀረቡ አስተያየቶች ላይ፣ አስፈላጊ | ፌብሩወሪ/ |

| | |
|---|---|
| ከሆነ ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የሥራ ክፍለጊዜ በመመደብ አማራጮችን ይመለከታል። | መግቢያ- እስከ ማርች-አጋማሽ* |
| አስፈላጊ ከሆነ እና ቦርዱ ሌሎች አማራጮች ካሉት አንድ ወይም የበለጠ የህዝብ አስተያየት መቀበያ ሁነቶችን ያካሄዳል። | ፌብሩወሪ - መገባደጃ |
| ስለ CIP ሬኮሜንዴሽኖች እና/ወይም የቦታ ምርጫ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ መልከአምድራዊ/ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ ፋሲሊቲ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት በቀረቡት የተለያዩ ሃሳቦች ላይ አስፈላጊ ከሆነ፣ ቦርዱ እርምጃ ይወስዳል። | ኤፕረል |
| የካውንቲው ካውንስል የስድስት-ዓመት የካፒታል ባጀት እና CIP ያፀድቃል። | ሜይ-መጨረሻ |
| የክላስተር PT(S)A ተወካዮች የሚመጣው CIP ወይም የ CIP ማሻሺያዎች በትምህርት ቤቶቻቸው ላይ ስለሚያደርሷቸው ተፅእኖዎች አስተያየቶችን ለትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ያቀርባሉ። | ጁን |
| የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንደንት በዚህ ወቅት ትምህርት ቤቶችን የሚመለከቱ ድርጊቶችን ማስተር ፕላን እና የወደፊት አስፈላጊ ነገሮችን የተቀናበረ መግለጫ ያዘጋጃል። | ጁላይ |

*አስፈላጊ ከሆነ ለሌላ ጊዜ የሚተላለፉ የእቅዶች ጉዳዮች ለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት የጊዜ ሠሌዳው ሊሻሻል ይችላል።

የሚዛመዱ ምንጮች፡- Code of Maryland Regulations §13A.01.05.07 and §13A.02.09.01-.03; Charter of Montgomery County, Maryland, Section 305; Montgomery County Code, Chapter 20, Article X, §§20-55 through 20-58

ስለ ደንቡ ታሪክ፡- ጊዜያዊ ደንብ/Interim Regulation፣ ጁን 1/2005፣ ማርች 21/2006 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 17/2006 ተሻሽሏል፣ ጁን 8/2008 ተሻሽሏል፣ ጁን 6/2015 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 11/2017 ተሻሽሏል፣ ሜይ 2/019 ተሻሽሏል።